## በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት
## ርዕስ መስተዳድር ጽ/ቤት
## ለዲያስፖራ የተዘጋጀ የመኖሪያ ቤት
## መሥሪያ ቦታ አሰጣጥ ደንብ

### 1. የደንቡ አስፈላጊነት

በተለያዩ ምክንያቶች ከትውልድ አገራቸው ወጥተው በውጭ አገራት የሚኖሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን የክልላችን ተወላጆች በክልላችን በሚካሄደው የልማትና የድህነት ቅነሳ እንቅስቃሴ አጋዥ ኃይል ማድረግ በማስፈለጉ፤

በውጭ አገራት የሚኖረው ተወላጅ በክልላችን በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆን ቀደም ብሎም ቢሆን ጥረት ሲደረግ የቆየ ቢሆንም አሁን ግን የሚሌኒየም በዓልን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም እየታየ ያለውን ወደ አገር ቤት የመመለስ መነሳሳት መደገፍ በማስፈለጉ፤

በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ-ኢትዮጵያውያን የክልሉ ተወላጆች በትውልድ አካባቢያቸው የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ እንዲያገኙ ለማስቻልና ይህንንም አሠራር በክልሉ ከተሞች ወጥ በሆነ መልኩ ለመምራት ሲባል ይህ በክልሉ ከተሞች የሚያገለግል የቦታ አሰጣጥ ደንብ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚህ መሠረት ይህ በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 66/6 መሠረት ደንብ ወጥቷል።

### 2. ዓላማ

የዚህ ደንብ ዋና ዓላማ ለዲያስፖራው የሚደረግ የቦታ አሰጣጥ ግልጽና ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግ በምላሹ ዲያስፖራው ክልሉን የሚጠቅም ተግባር እንዲያከናውን ማነሳሳት ነው። ይህን በማድረግ የክልሉን የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ሥራ ከዚህ ጋር አያይዞ ለመሥራት እንዲያስችል፤

2.1. በውጭ የሚኖረው የክልሉና የአገሪቱ ተወላጅ /ዲያስፖራው/ በዕውቀት፣ በካፒታልና በቴክኖሎጂ ሽግግር ክልሉን እንዲያግዝ ማነሳሳት፣

2.2. ከዲያስፖራው ጋር የበለጠ መቀራረብና መግባባትን መፍጠር፣ የአገር ገፅታ ከመቀየር አንፃር አስተዋፅኦ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

2.3. በከተሞቻችን ሞዴል ሊሆን የሚችል እና አገልግሎቶቹ የተሟሉለት የተሻለ ደረጃ ያላቸው ግንባታዎችን የያዘ የመኖሪያ መንደር መመስረት የሚቻልበትን አሰራር መዘርጋት ነው፡፡

2.4. በውጭ የሚኖረው የክልሉ ተወላጅ የክልሉን የመልማት አቅም መረጃ በመውሰድ የኢንቨስትመንት ማስተዋወቅ ሥራ እንዲሠራና ራሱም ኢንቨስት ለማድረግ እንዲነሳሳና እንዲወስን ነው፡፡

2.5. በክልላችን ያረጁ የከተማ አካባቢዎችን ለማደስ የተጀመረው ሥራ ዲያስፖራው በሚያደርገው የኮንስትራክሽን ሥራ ከተሞችንም እንዲያነቃቃ ለማድረግ ነው፡፡

## 3. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ "ዲያስፖራ" ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ በሌሎች አገራት ዜግነታቸውን ሳይቀይሩ ወይም ቀይረውና የሚኖሩበትን አገር ዜግነት ተቀብለው የሚኖሩ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ በግልፅ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ትውልደ-ኢትዮጵያውን ማለት ነው፡፡

## 4. አስተባባሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም

ወደ ክልሉ የሚመጡ የዳስፖራ አባላትን በተቀላጠፈና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማስተዳደር በየደረጃው የሚከተሉ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፡፡

1. በክልል ደረጃ

| | |
|---|---|
| ♦ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር | ሰብሳቢ |
| ♦ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| ♦ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ | አባል |

- የአዋሳ ከተማ የሽግግር አስተዳደር ከንቲባ አባል
- የማስታወቂያና ባህል ቢሮ ኃላፊ አባል
- በር/መ/ጽ/ቤት የህዝብና የውጭ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ደምፅ አልባና ፀሐፊ

2. በዞኖችና ልዩ ወረዳ /አባል/

- የዞን/ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ሰብሳቢ
- የሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ኃላፊ አባል
- የንግድና ኢንዱስትሪ መምሪያ ኃላፊ አባል
- ለዞን/ለልዩ ወረዳው ተጠሪ የሆነ ከተማ ከንቲባ አባል
- የማስታወቂያና ባህል መምሪያ አባል
- በዞን/በልዩ ዋረዳ አስተዳዳሪ የሚመደብ የዲያስፖራ አስተባባሪ ዩኒት ኃላፊ ድምፅ አልባና ፀሐፊ

## 5. የቦታ አሰጣጥ ስልቶች /መንገዶች/

በክልሉ ለዲስፖራው የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ አሰጣጥ በሁለት መንገድ ይከናወናል። ይኸውም በሚኖሩበት አገር የኢትዮጵያ ሚስዮን አማካይነት በማህበር በመደራጀት እና በተናጠል በግል በማመልከት ሊሆን ይችላል።

### 5.1. በማህበር ተደራጅተው ጥያቄ ለሚያቀርቡ

5.1.1. በማህበር ተደራጅተው ጥያቄ ለሚያቀርቡ በክልሉ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር አደረጃጀት ደንቡ የሚጠይቀውን መስፈርት እስካሟሉ ድረስ የቦታ ምሪት ጥያቄአቸውን የከተማ አስተዳደር ያለውን የቦታ አቅርቦትና ተፈላጊውን የቤት ደረጃ /Standard/ እያገናዘበ ያስተናግዳል።

5.1.2. በተለይም የከተማውን ደረጃ ለመጠበቅ G+1 እና በላይ የሆኑ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ የሚያከናውኑ ማህበራት እንዲበረታቱ ይደረጋል።

5.1.3. የዲያስፖራ አስተባባሪ ኮሚቴ በአንቀፅ 5.1.1. ከተቀመጠው ውጪ በውሳኔ ለዚሁ ዓላማ በተከለለ ቦታ ምደባ እንዲካሄድ ከወሰነ በአንደኛ ደረጃ ከተማ እስከ 300 ስኬር ሜትር፣ በ2ኛ ደረጃ ከተማ እስከ 350 ስኬር ሜትር፣ በ3ኛ ደረጃ ከተማ እስከ 400 ስኬር ሜትር፣ ከ1ኛ -3ኛ ደረጃ ካሉት ከተሞች ውጭ ባሉ ከተሞች እስከ 500 ስኬር ሜትር ለቦታው በተመደበው ዋጋ እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

## 5.2. በግል ወይም በተናጠል ለሚጠይቁ አመልካቾች

በዚህ ደንብ የተካተተ ማንኛውም የቤት መሥሪያ ቦታ ጠያቂ በሁለት መልኩ ሊስተናድ ይችላል።

5.2.1. በግል ማመልከቻ የቦታ ምሪት ለሚጠይቁ የዲያስፖራ አባላት እንደየፍላጎታቸውና እንደየአቅማቸው ለማስተናገድ ይቻል ዘንድ አቅም ያላቸው አመልካቾች አሁን በሥራ ላይ ባለው የሊዝ ሥርዓት መሠረት ይስተናገዳሉ።

5.2.2. በአንቀፅ 5.2.1.የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው ያለው የዲያስፖራ ኮሚቴ ሲያምንበትና ውሳኔ ሲያስተላልፍ በምደባ ለዚሁ ተብሎ በተከለለው ቦታ በተናጠል እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል።

5.2.3. በሊዝ የመግዛት አቅም የሌላቸውና በተናጠል የሚመጡ አመልካቾች አንቀፅ 5.2.2.ተፈፃሚ ካልተደረገ እንደማንኛውም ዜጋ ተራቸውን ጠብቀው በምሪት ቦታ የማግኘት መብታቸው ይጠበቅላቸዋል። ይህም የሚሆነው ከዚህ በፊት በስማቸው በምሪት ያገኙት ሌላ ቦታ አለመኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

# 6. የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች

ማንኛውም የከተማ አስተዳደር ይህን ተግባር በብቃትና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለማካናወን የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል፡-

6.1. በከተማው ፕላን ላይ የቦታ መረጣ ማድረግና የተመረጡ ቦታዎችን ሳይት ፕላን ማዘጋጀት፣

6.2. የቦታ ሽንሽና ጥናት ማካሄድ፣

6.3. የካሳ ክፍያ ግምት /ካለ/ ማድረግና ክፍያውን ማከናወን፣

6.4. የቅየሳ ሥራ ማከናወንና የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማዘጋጀት፣

6.5. ቦታ ፈላጊዎችን መመዝገብና ብቁ የሆኑትን መለየት፣

6.6. የተዘጋጅ ቦታዎችንና የቦታ ፈላጊዎችን ዝርዝር ለውሳኔ ለሚመለከተው አካል ማስተላለፍ፣

## 7. ቦታ ፈላጊዎችን መመዝገብ ፣ ማጣራትና ብቁ የሆኑትን መለየት

በዚህ ደንብ ትርጓሜ የተካተተና የደንቡ ተጠቃሚ የሆነን አንድ አመልካች በሚገባ ለመለየት እንዲቻል የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

7.1. ከሚኖርበት የውጭ አገር የኢትዮጵያ ሚሲዮን /ኢምባሲ/ በዚያ አገር ኗሪ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ፣

7.2. የፌዴራል ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብዳቤ ወይም የክልሉ መንግስት የዲያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ፣

7.3. ጉዳያቸውን ራሳቸው የማይከታተሉ ከሆነ የወኪላቸውን ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፣

7.4. በክልሉ ውስጥ በስማቸው ሌላ ቤት ወይም የቤት መሥሪያ ቦታ የሌላቸው ስለመሆኑና ያላቸው ሆነው ከተገኙ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ያለምንም ካሣና የመልስ ክፍያ መሬታቸውን እንደሚወስድ በማመልከቻው ላይ መተማመኛ መፈረም አለባቸው፡፡

7.5. በመሬቱ ለመገንባት ያሰቡትን ቤት ዲዛይን ወጪ 10% በባንክ በዝግ አካውንት ማስቀመጥ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡

## 8. ቦታ የማስረከብ ሂደት

8.1. የቦታ አሰጣጥ ሂደቱ በተቻለ መጠን ከቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረድ የፀዳና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ መመራት ይኖርበታል፤

8.2. ቦታ የተሰጣቸው አባላት ቦታውን በተረከቡ በ60 ቀናት /በሁለት ወራት/ ውስጥ የግንባታ ፕላናቸውን አቅርበው የግንባታ ፈቃድ መውሰድ አለባቸው፤

8.3. የግንባታ ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚስተናገዱ ብቻ እስከ ዘጠኝ /9/ ወራት ድረስ ግንባታ ማካሄድ ካልጀመሩ ያለተጨማሪ ማስጠንቀቂያ የወሰዱት ቦታ ለማዘጋጃ ቤቱ ገቢ ይደረጋል፤

8.4. የተወሰደውንም መሬት ማዘጋጃ ቤቱ ለሌላ ቦታ ጠያቂ ሊሰጠው ይችላል፤

8.5. ዲያስፖራውን ለመሳብ ተብሎ በልዩ ሁኔታ በዚህ ደንብ አግባብ የተሰጠ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ ላይ ግንባታ ሳይካሄድበት መሸጥ፣ በስጦታ ማስተላለፍ እና በሞት ምክንያት ከሚከሰት ውርስ በስተቀር ማውረስ አይፈቀድም።

## 9. ደንቡ ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ በውይይት ጸድቆ ከወጣበት ከዛሬ ሐምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ በመ/ም/ቤት የጸና ይሆናል።

ሺፈራው ሽጉጤ
የደቡብ ብ.ብ.ሕ.ክ.መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር